# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

# Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

http://www.kinijitethiopia.org
e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

***ድርጅታዊ መግለጫ*** ***ግንቦት 15፣1999***

## ከጁን 16-24 2007 የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር በአውስትራሊያ የተለያዩ ከተሞች ከኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ ለማድርግ ሰለአቀዳቸው ስብሰባዎች በሚመለከት የተሰጠ መግለጫ::

ወደ አውስትራሊያ ክፍለ አለም ቅንጅት ፊቱን ሲያዞር ይህ የመጀመሪያው ነው:: ይሁንና በቅንጅት የተወከለ ግለሰብ በመዘዋወር በአውስትራሊያ እንቅስቃሴ ባያደርግም በአውስትራሊያ የሚገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በተናጠልም ይሁን በቡድን በተደራጀ መንገድ ይህንን ህዝባዊና ሃገራዊ አላማ ከመደገፍ የቦዘኑበት ወቅት አልነበረም:: አሁንም በቅንጅት የድጋፍ አካላት አስተባባሪነት በተለያዩ የአውስትራሊያ ከተሞች በመዘዋወር የቅንጅት አለም አቀፍ አመራሮች በቅርቡ የሚያደርጉት ስብሰባ ዋና አለማ ይህንን በተለያዩ መንገዶች ሲሰጥ የነበረውን ድጋፍ በተጠናከረ፣ አንድ ወጥነት ባለው፣ በከፍተኛ ህዝባዊ አሳታፊነት፣ ግልጽነትና ህዝባዊ ተጠያቂነት ላይ ወደ ተመሰረተ ጠንካራና ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት የመቀየር ይሆናል:: ይህንን በማድረግ አውስትራሊያ ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሌሎች ክፍለ-አለማት እንደሚገኙ ወገኖቻቸው፣ በሙሉ ሃይላቸው በመንቀሳቀስ በሁሉም መስኩ የሃገራችን ህዝብ የሚያደርገውን የነጻነትና የዴሞክራሲ ትግል ለማገዝ፣ ቅንጅትም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጥልባቸውን ሃላፊነትና አደራ መወጣት እንደሚችሉ ጽኑ እምነት አለን::

የአለም አቀፍ አመራሩ ጉብኝት አላማ በአውስትራሊያ አህጉር ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የሃገራችንን ህዝብ ነጻነትንና ዴሞክረሲን እንዲላበስ፣ ከድህነትና ከመከራ እንዲወጣ፣ ሃገሩን ጥሎ የሚሰደደው በሃገሩ ተከብሮና ተረጋግቶ እንዲኖር፣ ሃገሩን ጥሎ የተሰደደው ከተበተነበት ተመልሶ የሚወዳትንና ቀደምቶቹ በብዙ መስዋእትነት የተዉለትን የነጻነትና የታሪክ ባላጸጋ ሃገሩን እንዲታደግ፣ ዘረኛነት እንዲያከትም፣ በሃገራችን የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲያብብ፣ በቅንጅት የአሳታፊነት፣ የግልጽነት የዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሰረተ የድጋፍ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችልበትን፣ ብዙሃኑ በያገባኛል ስሜት የሚሳተፉበትን፣ ብዙሃኑ በመረጡት የሚወከሉበትን የአደረጃጀት መሰረት ለመጣል ነው::

ዛሬ በአለም ላይ የሚገኙ የቅንጅት ሀገራዊ ይሁኑ አህጉራዊ የድጋፍ ድርጅቶች፣ የቅንጅትን ፖለቲካ የሃገር ማዳን ፖለቲካ እንጂ የርእዮተ ዓለም መፏከቻ፣ የስልጣን ማማ ላይ መፈናጠጫ አድርገው በማያዩ፣ ለሃገራቸውና ለህዝባቸው ከፍተኛ ፍቅር ባላቸው፣ ብዙሀንን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በማሳተፍ የተቋቋሙ ናቸው:: እነዚህ የድጋፍ ድርጅቶችና አባላቶቻቸው የተሳሰሩበት የዴሞክራሲና የሃገር ፍቅር ቃል ኪዳን በያሉበት ጠንካራ የአትዮጵያውያን ማህበረሰብ መፍጠሪያ፣ ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ዘላቂነትና ቋሚነት ካላቸው ሃገርና ህዝብ ጋር የተሳሰሩ እንዲሆኑ ቅንጅት ባለው ራእይ ላይ ተመስርተው እየተጠናከሩ በመሄድ ላይ ናቸው:: በአውስትራሊያም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ክፍለ አለማት እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው ጎን ለመቆም የሚችል ስፋትና ጥልቀት ያለው፣ ሃገርና ወገንን በማስቀደም የሚንቀሳቀስ ጠንካራ አደረጃጀት በቅንጅት ራእይና መርህ ላይ ተመስርተው ማቋቋማቸው በወያኔ/ኢህአዴግ አፈና ተደፍቆ በውጭ በሚኖረው ኢዮትዮጵያዊ ወገኑ ላይ ትልቅ ተስፋ ለጣለው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ሃገራቸውንና ወገናቸውን ሲሉ ዛሬ በወያኔ/ኢህአዴግ እስር ቤት ውስጥ በግፍ ታስረው፣ ለሚሰቃዩት የቅንጅት መሪዎች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የጋዜጠኞችና ለሎችንም የፖለቲካ እስረኞች አለኝታ እንደሚሆን አንጠራጠርም::

በመሆኑም ዝግጅቱ በሚደረግባቸው በአውስትራሊያ ከተሞች የምትገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በተዘረጋው ፕሮግራም መሰረትና ፍጹም ቅንጅታዊ በሆነ የግልጽነትና የዴሞክራሲያዊነት መርህ አማካይነት በሚደረጉት ስብሰባዎች ላይ በመገኘት የስብሰባው ዓላማ የተሳካ እንዲሆን ንቁ ተሳትፎ እንድታደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

***ቅንጅት ለዴሞክራሲ ለነጻነት ለእኩልነትና ለአንድነት የሚቆሙ የኢትዮጵያውያን ቤት ነው::***
***ቅንጀትን ማጠናከር ይህንን የኢትዮጵያውያንን የጋራ ቤት ማጠናከር ነው::***

***ቅንጅ ዓለም አቀፍ አመራር***
***ግንቦት 15 ቀን፣ 1999***
***ሜይ 23 ቀን፣ 2007***


Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701 Silver Spring MD, 20911 USA
Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974 www.kinijitethiopia.org